# ራስን ለመገምገም የሚያገለግል የደረጃዎች ሰንጠረዥ

| | A1 | A2 | B1 | B2 | C1 | C2 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የመረዳት ሁኔታ<br><br>ሰምቶ የመረዳት ችሎታ | የተለመዱ ቃላትና በጣም ቀላል የሆኑ ሐረጎችን መለየት እችላለሁ። ለመለየት የምችለው ደግሞ ተናጋሪው ሰው ሳይቸኩልና በብሩኅ አነጋገር ሲናገር ነው። | ስለ ግል ሁናቴዎቸ ሲናገሩ የሚጠቀሙት ሐረጎችና ቀላል የሆኑ ቃላትን ልረዳ እችላለሁ። ግል ሁናቴዎቸ ማለት ለምሳሌ ራሴና ቤተሰቤ ፡ የቅርብ አካባቢየና የሰርክ ህይወቴ እንዲሁም ስለ ስራ መቀጠር የመሳሰሉትን ያካተተ ነው። የአጭርና ግልጽ የሆነ መልእክት ፍሬ ነገር አብዛኛው ይገባኛል። | በተለያዩ ቦታዎች፡ ለምሳሌ መስርያ ቤት፡ ትምህርት ቤት፡ በእረፍት ጊዜ መዝናኛ ቦታዎች ወ ዘ ተ ሰው በተደጋጋሚ የሚነጋገርባቸው አረእስቶች ላይ ያተኮረ ውይይት አብዛኛው ይገባኛል። ሳይቸኩሉ ብሩኅ በሆነ አነጋገር ከተናገሩ፡ ብዙዎቹን የተለቪዠንና የሬድዮ ፕሮግራሞችን መከታተል እችላለሁ። | ረዘም ያለ መግለጫ፡ ለምሳሌ የአስተማሪ ለክቸር፡ ይገባኛል። አርእስቱን የማውቀው ከሆነ ውስብስብ የሆነ ክርክርን መከታተል አያዳግተኝም። በተለቪዠን የሚቀርበው ዜና አብዛኛው ይገባኛል። የተለመደውን ቋንቋ የሚጠቀም ፊልምም ኣብዛኛው ይገባኛል። | ይበልጥ የዳበረ ቋንቋው፡ ግልጽ አወቃቀር ባይኖረውም እንዲሁም አግባቡ በጕልህ የተገለጸ እንኳን ባይሆን፡ ሊገባኝ ይችላል። የተለቪዥን ፕሮግራምና ፊልም ያለ ብዙ ችግር ልከታተል እችላለሁ። | ሰው የሚናገረው ወይም ከተለቪዥን ወይም ከራድዮ ወይም ከፊልም የምሰማው ንግግርን ለመረዳት ምንም አይነት ችግር የለኝም። ባካባቢው የሚነገረው ዘዬን ከተለማመድኩ፡ ያገሩ ተወላጅ የሆነ ሰው እየተጣደፈ ቢናገርም መረዳት አያቅተኝም። |
| ጽሁፍን የመረዳት ችሎታ | ለምሳሌ የማስታወቅያ ሰሌዳ ወይም ረክላም ወይም ማውጫ (ካታሎግ) ላይ የተጻፉ ተለመዱ ስሞችና ቃላት እንዲሁም በጣም ቀለል ያሉ አረፍተ ነገሮችን መለየት እችላለሁ። | ቀለል ያሉ አጫጭር ጽሁፎችን ማንበብ እችላለሁ። ከረክላም፡ መረጃ ሰነዶች፡ የሬስቶራንት የምግብ ዝርዝር ወይም ከጊዜ ሰንጠረዥ ከመሳሰሉት የጽሁፍ አቅርቦቶች፡ የሚያስፈልጉኝ አንዳንድ መረጃዎችን፡ ለማውጣት እችላለሁ። | በሰርክ ሕይወትና በስራ ቦታ ሰው አዘውትሮ በሚጠቀምባቸው ቃላት የተጻፈ ጽሁፍ ሊገባኝ ይችላል። ስለ አንዳንድ ያጋጠሙ ነገሮች የተጻፈ መግለጫና የግል ደብዳቤ ውስጥ የተጻፈ የስሜትና የፍላጎት ይዞታም ይገባኛል። | ወቅታዊ በሆነ አርእስት የተጻፉና ዝንባሌዎችና አስተያየቶችን ያካተቱ ጽሁፎች (አርቲክሎች) እንዲሁም ሪፖርቶችን ማንበብ እችላለሁ። ወቅታዊ የሆነ በስድ ንባብ የተጻፈ ስነ ጽሁፍን ማንበብ አያስቸግረኝም። | በማያከራክር የሞያ አርእስት የተጻፈ ረዘም ያለ ጽሁፍ ይገባኛል። በስነ ጽሁፍ ደረጃ የቀረበም ይገባኛል። የተለያዩ ዘይቤዎችን መለየት እችላለሁ። የሞያ አዘል ስነ ጽሁፍና ረዘም ያለ የመረጃ ጽሁፍም ፡ ከራሴ ተሞክሮና ፍላጎት ውጭ ቢሆንም ይገባኛል። | በጽሁፍ የሚቀርብ ይዞታ ሁሉ ያለ ምንም ችግር ይገባኛል። ለምሳሌ፡ ይዞታው ረቂቅ የሆነ ስነ ጽሁፍ፡ ወይም መዋቅሩ ውስብስብ የሆነ እንደ ሞያ ጽሁፍ አይነቱን መረዳት አያስቸግረኝም። |
| መናገር<br><br>መወያየት<br><br>በመናገር ሃሳብን የመግለጽ ችሎታ | ከኔ ጋር የሚነጋገረው ሰው ሳይቸኩል ለመናገር ፌቃደኛ ከሆነና ሳይገባኝ ሲቀር ሊደጋግመው ወይም በሌላ አነጋገር ሊሞክር ፈቃደኛ ከሆነ፡ በቀላል ደረጃ መናገር እችላለሁ። ቀለል ያሉ ጥያቄዎችም ራሴ መጠየቅና የተጠየቅኩትን መመለስ እችላለሁ። | በቀላል ኣያያዝ የቀላል መረጃ ማስተላለፍ ብቻ በምያስፈልግበት ጊዜ፡ ንግግሩ ላይ ለመካፈልና ተዘውትሮ የሚሰራ አይነት ስራ ላይም መካፈል እችላለሁ። አጠር ላለ ጊዜ ማህበራዊ ውይይት ላይ መካፈል እንኳን ብችል፡ የመረዳት አቅሜ ዝቅተኛ በመሆኑ፡ ውይይቱን ማንቀሳቀስ አልችልም። | ቋንቋው ወደ ሚነገርበት ኣገር ወይም ክፍለ ሀገር የተጓዝኩ እለት፡ አብዛኞቹ የሚያጋጥሙኝ ሁኔታዎችን መቋቋም እችላለሁ። ፍላጎቴን በሚቀሰቅስ አርእስት በሚደረገው ውይይትም ያለ አንዳች ዝግጅት መካፈል እችላለሁ። እንዲሁም አርእስቱ በኑሮ፡ ለምሳሌ፡ ቤተሰብ፡ የእረፍት ጊዜ ማዝናኛ፡ ስራ፡ ጉዞ፡ ዜና ላይ ያተኮረ ከሆነ፡ | ስወያይና ስከራከር ቀልጣፋ በመሆኔና የሚያግተኝ ነገር ባለመኖሩ፡ ካገሩ ተወላጆች ጋር ያልተጋነነ ግንኙነት ይኖረኛል። የታወቀ አርስት ላይ በሚደረግ ውይይት ንቁ ተሳተኣፊ ሆኘ፡ ያለኝን ኣቅዋም ማስረዳትና መከላከል እችላለሁ። | ያለ ዝግጅት ቀልጠፍ ባለ አነጋገር ሳልንተባተብ ሀሳቤን መግለጽ እችላለሁ፥ እንደየሁኔታው ቋንቋውን ለማኅበራዊና እንዲሁም ለሞያና ለጥቅም-አዘል ጉዳዮች ልጠቀምበት እችላለሁ። ጭብጦችና አቋሞችን በትክክል የመግለጽ ችሎታ አለኝ። አቀራረቡን ለአዳማጬ እንዲስማማ ማድረግም እችላለሁ። | የሆነ አይነት ውይይት ወይም ክርክር ላይ ያለ አንዳች ችግር መካፈል እችላለሁ። ሀሳቤን ለመግለጽ፡ በተራ ቋንቋ ወይም ፈሊጦችን የመጠቀም ዕድልን መምረጥ እችላለሁ። ሳል እንተባተብ ሀሳቤን የመግለጽና ጥቃቅን ልዩነቶችን በትክክል የማስተላለፍ መጠነኛ ችሎታም አለኝ። ይህ እንዳለ ሆኖ ችግር ብያጋጥመኝ፡ ሰው ችግሬን ሳያስተውለው አማራጭ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የውይይቱ ተካፋይ እሆናለሁ። | | | ቃላትን በመጠቀም መፍትሄ ኣመጣለሁ፥ |
| በመናገር ስራን ያማካሄድ ችሎታ | ቀለል ያሉ ሐረጎች ወይም አረፍተ ነገሮችን በመጠቀም አንዳንድ ነገሮች፡ ለምሳሌ የት እንደምኖር ወይም ስለ ማውቃቸው ሰዎች በመጠኑ ለመግለጽ እችላለሁ። | የተለያዩ ሐረጎችና አረፍተ ነገሮችን በመጠቀም ቀለል ባለ መንገድ ስለ ቤተሰቤና ስለ ለሎች ሰዎች፡ ስላለኝ ትምህርት እንዲሁም ስለ ቀድሞውና ስለ ያሁኑ ስራዬ መግለጽ እችላለሁ። | ስለ ተሞክሮዎችና ኣጋጣሚዎች፡ ስላሉኝ ህልሞች፡ ስላለኝ ተስፋና የመጪው ጊዜ እቅዴን ለመግለጽ፡ ሐረጎችን ቀለል ባለ ዘዴ አዛምዳለሁ። ስላለኝ አስተያየትና እቅድ አጠር ያለ ምክንያትና መግለጫን መስጠት እችላለሁ። ታረክ መተረክ እችላላሁ፡ መጽሀፍ ላይ ያነበብኩትንና ፊልም ውስጥ ያየሁትንታሪክ መልሸ ማውራት እችላለሁ፡ ያሳደረብኝ ስሜትንም መግለጽ እችላለሁ። | ፍላጎቴን በሚቀሰቅስና ተሞክሮ ባለኝ አርእስት ብሩህና ዝርዝር በሞላው አኳኃ ን መግለጽ እችላለሁ። ስለ አንድ አቋም መግለጽና አቋሙ ያሉትን አዎንታዊና አሉታዊ ገጽታዎችን ከነ አማራጮ ቹ ማቅረብ እችላለሁ። | ተጓዳኝ ባህርይ ያለው ውስብስብ የሆነ ነገር በብሩህና በዝርዝር መግለጽ እችላለሁ። አንዳንድ ነጥብ ላይ ተጨማሪ መግለጫ ከመስጠት አልፎ፡ ፍሬ ነገሩን በማጠቃለል የመደምደምያ ቃልም ልሰጥ እችላላሁ። | ከሁኔታው ጋር በሚጣጣም ኣኳኃን ብሩኅና ልቅ የሆነ መግለጫ ወይም ክርክርን ማቅረብ እችላለሁ። ኣዳማጬ አንገብጋቢ ነጥቦችን ለመገንዘብና ለማስታወስ እንዲችል፡ ስኬታማ የሆነ ሎጂካዊ መዋቅርን መጠቀም እችላለሁ። |
| መጻፍ<br><br>በጽሑፍ ሐሳብን የመግለጽ ችሎታ | ቀለል ያሉና አጫጭር የሆኑ መልእክተች፡ ለምሳሌ የሰላምታ ካርድን መጻፍ እችላለሁ። ለምሳሌ፡ ስሜ አድራሻዬ እንዲሁም ዜግነቴን የመሳሰሉ የግል መረጃዎችን ቀላል ፎርም ላይ መሙላት እችላለሁ። | ቀለል ያሉ አጫጭር መልእክቶችን መጻፍ እችላለሁ። ማስታወሻ መጻፍም አያዳግተኝም። ለምሳሌ፡ ቁም ነገር የዋለልኝ ሰውን ለማመስገን ቀለል ያለ አጭር የግል ደብዳቤም ልጽፍ እችላለሁ። | በማውቀው ወይም ፍላጎቴን በሚቀሰቅስ አርእስት ያተኮረ ቀለል ያለ አጭር ጽሁፍን መጻፍ እችላለሁ። ስሜቶችና ግንዛቤዎችን የሚገልጽ የግል ደብዳቤን መጻፍ እችላለሁ። | ስሜቴን በሚቀሰቅስ አርእስት ብሩህና ዝርዝረ የሞላው ጽሁ ፍን ማቅረብ እችላለሁ። መረጃ የሚሰጥ ወይም አንድ አቋምን የሚደግፍ ወይም የሚቃወም ድርሰት ወይም ሪፖርትን መጻፍ እችላለሁ። ኣጋጣሚዎችና ተሞክሮዎች ለአንድ ሰው ያላቸውን ትርጉም አጕልቶ የሚያሳይ ደብዳቤን መጻፍ እችላለሁ። | በዝርዝር የተቀመጡ አመለካከቶችና መግለጫዎች በመስጠት ብሩህና ጥሩ መዋቅር በያዘ ጽሁፍ ሃሳቤን መግለጽ እችላላሁ። ስለ ተወሳሰቡ ሁኔታዎች ደብዳቤ ወይም ድርሰት ወይም ሪፖርትን በመጻፍ፡ አንገብጋቢ ለሚመስሉኝ ነጥቦችን መከራከር እችላለሁ። ጽሁፉ ለአንባቢው ተስማሚ እንዲሆን ለማድረግ ምቹ ዘይቤ ልጠቀም እችላላሁ። | አጻጻፉ ከወቅቱ ጋር በሚስማማ ሁኔታ ብሩኅና ልቅ የሆነ ጽሁፍን ማቅረብ እችላለሁ። በአንድ አርእስት ይዞታው ውስብስብ የሆነ ደብዳቤ ወይም ሪፖርት ወይም አርቲክልን መጻፍ እችላለሁ። ጽሁፉ ሎጂክ በተከተለ መንገድ ስለሚቀርብ፡ አንባቢው አንገብጋቢ ነጥቦችን መገንዘብና ማስታወስ ይችላል። በሞያ አዘል ጽሁፍ ይሁን በስነ ጽሁፍ፣ መደምደምያና አጭር የማጠቃላያ ጽሁፍን ማቅረብ እችላላሁ። |